በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ኦርቶዶክሳዊ - ቤተሰብ
# ክፍል አሥር


## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


***ቦታ፦*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ነሐሴ ፬ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

## ልጆች ወላጆቻቸውን እንዴት ሊወዱ ይገባቸዋል?

***ለወላጆች በመታዘዝ***

- ወላጆቻችንን የመውደዳችን አንዱ ምልክት መታዘዝ ነው፡፡ መታዘዝ ማለት ቃላቸውን ማክበር ብቻ ሳይሆን የአስተሳሰብ አቅጣጫቸውን መከተል ነው፡፡ በሕይወት ቢኖሩም ባይኖሩም ልንታዘዛቸው ይገባናል፡፡
- ወላጁን የማያከብር የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ይጥሳል፡፡
- ‹‹*ልጆች ሆይ፥ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ፥ ይህ የሚገባ ነውና፡፡*›› ***ኤፌ 6፡1፡፡*** እንደተባለው ከእግዚአብሔር ሕግ ጋር እስካልተጋጨ ድረስ ወላጆችን በሁሉ ልንታዘዛቸው ይገባናል፡፡
- *መጽሐፍ ቅዱስ ሄሮድያዳ ለእናትዋ በታዘዘችበትና ፈቃድዋንም በሄሮድስ በኩል* ‹‹እርስዋም በእናትዋ ተመክራ፡፡ የመጥምቁን የዮሐንስን ራስ በዚህ በወጭት ስጠኝ፡፡›› ***ማቴ 14፡8፡፡*** በማለት እንዳስፈጸመችው ባለ *መንገድ* እንድንታዘዝ አይመክረንም፡፡
- ልጆች እንዲዋሹ፣ ለእግዚአብሔር እንዳይታዘዙ፣ ከጾምና ከጸሎት እንዲርቁ፣ ወይም በማንኛውም ከእግዚአብሔር እንዲርቁ በሚጠየቁበት አጋጣሚ ለወላጆቻቸው ይታዘዙ አንልም፡፡
- ነገር ግን ጠቢቡ ሰሎሞን እናቱን ከዙፋኑ ተነስቶ እጅ ነስቶ (ሰግዶ) እንደተቀበላት እንዲያደርጉና ‹‹*እርስዋም፦ አንዲት ታናሽ ልመና እለምንሃለሁ አታሳፍረኝ፡፡*›› ብላ ሱነማዊቱ አቢሳ ለወንድሙ ለአዶንያስ እንድትዳርለት ስትጠይቀው ግን ‹‹*ንጉሡም፡፡ እናቴ ሆይ፥ ለምኚ አላሳፍርሽምና አላት፡፡*›› ***ቀዳ ነገ 2፡20፡፡*** የተባለው ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሳይተላለፍ አይሆንም እንዳለ እናድርግ፡፡ ልጅ የአባቱን ሚስት እንዴት ያገባል?

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

***ለወላጆች በመታዘዝ…***

- ልጆች ሆይ ይስሐቅ ለአባቱ ለአብርሃም እንደታዘዘው ለወላጆቻችን እንታዘዝ፡፡
- እግዚአብሔር ልጁን ይሰዋለት ዘንድ አብርሃምን ሲጠይቀው ይስሐቅም ከአባቱ ጋር በማለዳ በመነሣት፣ በፍጹም መታዘዝ እንደተከተለው ታዘዙ፡፡
- አህዮቹን መምራት ትቶ የመሠዊያውን እንጨት እንዲሸከም ሲጠየቅ ይስሐቅ አልተቃወመም፡፡
- አብርሃም መሠዊያውን አዘጋጅቶ ይስሐቅን በመሰውያው ላይ ባስተኛውና ይሰዋውም ዘንድ ቢላውንም ሲያነሳው ይስሐቅ የተቃውሞ ቃል ከአንደበቱ አልወጣም፡፡
- አብርሃም ለእግዚአብሔር ይስሐቅም ለአባቱ ለአብርሃም ከነበረው መታዘዝ የተነሣ የእግዚአብሔር መልአክ ከሰማይ አብርሃምን «በብላቴናው ላይ እጅህን አትዘርጋ፥ አንዳችም አታድርግበት፡፡» ***ዘፍጥ 22፡12፡፡*** ብሎታል፡፡ የመታዘዝ ልጅ እድሜው በምድር ላይ እንዲረዝም መጽሐፍ ቃል ገብቶልናልና፡፡
- ይስሐቅ ካደገም በኋላ ለአባቱ ለአብርሃም ታዛዥ ነበር፡፡ ይስሐቅ ለአቅመ አዳም ሲደርስ ለጋብቻም ሲዘጋጅ አብርሃም ሊያገባት የሚገባውን በነገረው መሠረት ታዞ ፈጽሞታል፡፡ ታዲያ ይስሐቅን እግዚአብሔርን ካልታዘዙት ብዙ ሕዝብ ጋር እንዴት እናነጻጽረዋለን?
- ስለ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስም ለእናቱ ለእመቤታችንና ለጠባቂዋ ለቅዱስ ዮሴፍ ይታዘዝ እንደነበር ተነግሮናል፡፡
- አምላካችን ፍጥረቱ የምትሆን እርስዋን እናቱ እንድትሆነው ፈጥሯታልና ለእርስዋ መታዘዙ እጅግ የሚደንቅ ነው!!!

# <u>በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች</u>

***<u>ቅጣታቸውንም በመቀበል</u>***

- ልጆች ለወላጅ ሊያሳዩት የሚገባው ፍቅር ምክራቸውንና ትእዛዛቸውን በመቀበል ብቻ የሚገለጽ አይደለም፤ ሲቀጡን (ሲገስጹን) የቅጣታቸው (የተግሳጻቸው) መጠን ምንም ይሁን ምን በደስታ በመቀበልም ጭምር እንጂ!

1. *<u>በቅጣት ውስጥ ፍቅር ይገለጻል</u>*

- እግዚአብሔር ሰውን ወዶ በአምሳሉ ፈጥሮታል፣ ሥልጣንን ሰጥቶታል፣ በሕይወታችን በእያንዳንዱ ሂደት ይጠብቀናል፣ በፍቅርም ይገስጸናል።
- *<u>በዕብ 12፡6</u>* ‹‹ልጄ ሆይ፥ የጌታን ቅጣት አታቅልል፥ በሚገሥጽህም ጊዜ አትድከም፤ ጌታ የሚወደውን ይቀጣዋልና፥ የሚቀበለውንም ልጅ ሁሉ ይገርፈዋል ብሎ የሚነጋገረውን ምክር ረስታችኋል።››፣ *<u>ምሳ 3፡12</u>* ‹‹እግዚአብሔር የወደደውን ይገሥጻልና፥ አባት የሚወድደውን ልጁን እንደሚገሥጽ።›› እንደተባለ
- እግዚአብሔር ቅዱሳኑን ይጠብቃቸው ዘንድ ገስጿቸዋል።
- ልበ አምላክ ዳዊት እግዚአብሔር ሲገስጸው ‹‹መገሠጽስ እግዚአብሔር ገሠጸኝ ለሞት ግን አልሰጠኝም።›› *<u>መዝ 117 (118)፡18።</u>* በማለት ዘምሯል።
- እግዚአብሔር በታላቅ ፍቅሩ በታናሽ እስያ የነበሩትን መላእክት (አለቆች) በራእየ ዮሐንስ እንደተገለጸው ገስጿቸዋል። ለሎዶቅያው ቤ/ክ አለቃ ‹‹እኔ የምወዳቸውን ሁሉ እገሥጻቸዋለሁ እቀጣቸውማለሁ፤ እንግዲህ ቅና ንስሐም ግባ።›› *<u>ራእ 3፡19።</u>* እንዳለው።

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

***ቅጣታቸውንም በመቀበል…***

1. ***በቅጣት ውስጥ ፍቅር ይገለጻል…***

- ስለዚህ መለኮታዊ ተግሳጽ ታላቅ ጸጋ ነው፤ ይህ የተሰጠውንም ሰው እናከብረዋለን፡፡ ‹‹እነሆ፥ እግዚአብሔር የሚገሥጸው ሰው ምስጉን ነው ስለዚህ ሁሉን የሚችለውን የአምላክን ተግሣጽ አትናቅ፡፡›› *ኢዮ 5፡17፡፡* እንዳለ፡፡
- ወላጆች ለልጆቻቸው ባላቸው ፍቅር እግዚአብሔርን ይመስሉታል - ለልጆቻቸው ጥቅምና መዳን ሲሉ ይገስጿቸዋልና፡፡ ጠቢቡ ሰሎሞን ‹‹በበትር ከመምታት የሚራራ ሰው ልጁን ይጠላል ልጁን የሚወድድ ግን ተግቶ ይገሥጻዋል፡፡›› *ምሳ 13፡24፡፡*

2. ***የወላጆቻችንን ተግሳጽ በመቀበላችን ለእግዚአብሔር መታዘዛችንን እንገልጻለን***

- ተግሳጽ ለሰው ዘር ሁሉ አስፈላጊው ስለሆነ እግዚአብሔር ተግሳጽን እንቀበል ዘንድ አዞናል፡፡
- በመጽሐፈ ምሳሌ 1፡8 ‹‹ልጄ ሆይ፥ የአባትህን ምክር ስማ፥ የእናንትህንም ሕግ አትተው፡፡›› *ምሳሌ 1፡8፡፡* ፤ ‹‹እናንተ ልጆች፥ የአባትን ተግሣጽ ስሙ፥ ማስተዋልንም ታውቁ ዘንድ አድምጡ፡፡›› *ምሳ 4፡1፡፡* በማለት በመለኮት ኃይል የተገለጠውን የጥበብ ቃል እናገኛለን፡፡

3. ***ተግሳጽን በመቀበላችን ጥበብን እንጎናጸፋለን***

- ጠቢቡ ሰሎሞን ‹‹እናንተ ልጆች፥ የአባትን ተግሣጽ ስሙ፥ ማስተዋልንም ታውቁ ዘንድ አድምጡ፡፡›› *ምሳ 22፡15*፣ ‹‹እናንተ ልጆች፥ የአባትን ተግሣጽ ስሙ፥ ማስተዋልንም ታውቁ ዘንድ አድምጡ፡፡›› *ምሳ 19፡20፡፡* እንዳሉን ጥበብን ልናገኝ ከወደድን ጥበብ የምትገኘው ተግሳጽን በመቀበል ውስጥ ነው፡፡

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

***ቅጣታቸውንም በመቀበል…***

4. ***ተግሳጽን በመቀበል ባለጠግነትና ድል አድራጊነት ይገኛል***

- መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹ድህነትና ነውር ተግሣጽን ቸል ለሚሉ ነው ዘለፋን የሚሰማ ግን ይከብራል፡፡›› *ምሳ 13፡18*፣ የሚለን ሲሆን እግዚአብሔር ‹‹ተግሣጼን እንጂ ብርን አትቀበሉ፥ ከምዝምዝ ወርቅም ይልቅ እውቀትን ተቀበሉ፡፡›› *ምሳ 8፡10፡፡* በማለት ተናግሮናል፡፡
- ቅዱሳን ከክብር ይልቅ ተግሳጽን ይሹት ነበር፤ምክንያቱም ተግሳጽ ሰማያዊ በረከት ክብርም ሞትና ውድቀትን እንደሚያስከትሉ ያውቃሉና፡፡
- ይህን አስመልክቶ ቅዱስ ሰፈርኒቁ ‹‹የሻማ ብርሃን በእሳት ፊት እንደሚደክም ሁሉ የሰውም ነፍሱ በከንቱ ውዳሴ ትደክማለች፡፡›› በማለት ተናግሯል፡፡
- ወገኖቼ ሆይ! ማንም ሲያመሰግናችሁ ከርሱ ሽሱ እንጂ ስለምስጋናው ደስ አይበላችሁ፡፡ በዚህም ፈንታ በተግሳጻችሁ ጊዜ ደስ ይበላችሁ፡፡
- በአንድ ወቅት አንድ መነኩሴ አበምኔቱን ገዳሙን ለቆ ወደ ሌላ ገዳም ለመሄድ ይጠይቃቸዋል፡፡ አበ ምኔቱም ስለምን ይህን ታደርጋለህ ብለው ሲጠይቁት ‹‹በዚህ ምንም የሚያደክም ሥራና ፈተና የለም፡፡ በዚህ ገዳም የሚገኙም ሁሉ ቅዱሳን ናቸው፤ እኔ ግን ታላቅ በደለኛ ነን፡፡ እንዲህ ባለው መንገድ ኃጥእ ይድናልና የምገሰጽበትን ሥፍራ ፈልጌ አገኝ ዘንድ እሻለሁ፡፡›› ብሎ መልሶላቸዋል፡፡

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

***ቅጣታቸውንም በመቀበል…***

4. ***ተግሳጽን በመቀበል ባለጠግነትና ድል አድራጊነት ይገኛል…***

- ወገኖቼ ሆይ! ስለቅድስናዋ፣ ንጹሕ ስለሆነው ልቦናዋ፣ በጸሎትና በስግደትም ብዛት ጣጦችዋ እስኪያልቁ የደረሰችውን በሰው ፊት እብድ በመምሰል ትቀርብ የነበረችውን የቅድስት አናሲሞንን ገድልእናውቃለን? መከራን ከመቀበል ይልቅ እከበርበታለሁ ብላ በማሰብ የማይገባ ክብርን ከመቀበል ርቃ በመከራና ሕዝቡም እንደ ተራ አድርገው ሲቆጥሯት በማየት ትደሰት ነበር፡፡
- የሚያመሰግነን ሁሉ የሚወድደን አይደለም፡፡ ይልቁኑ የሚገስጸን ግን የሚጠነቀቅልንና የሚወደን ነው፡፡ የወይን ዛፍ ፍሬ ያፈራ ዘንድ መገረዝ እንደሚያስፈልገው ሁሉ የሰውም ነፍስ ፍሬ እንድታፈራ መገረዝ - ተግሳጽ ያስፈልጋታል፡፡
- በዚህም መንገድ ክፉ ልምዶች፣ ጊዜያችንን ጉልበታችንንና ስሜታችንን የሚያጠፉብን ነገሮች ሁሉ ተገርዘው ተቆርጠው በመልካም ፍሬያትና በጎ ምግባራት ይተካሉ፡፡
- የወይን ግንድ በወይኑ ባለቤት መገረዝን ለፍሬው መልካምነት ሲባል እንደሚቀበለው ሁሉ ልጆችም የወላጆቻቸውን ትእዛዝ ብዙ መልካም ፍሬ ማፍራት ያስቻለቸው ዘንድ ሊቀበሉ ይገባቸዋል፡፡

# ይቆየን፡፡

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org